# የኤፍሬም ይሳቅ ቡድን ከቀድሞ የኦነግ አመራር ጋር

በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳቅ የሚመራ አንድ ቡድን ከቀድሞ የኦነግ አመራር ጋር ባለፈው ሴፕቴምበር 19 - 21, 2008 (እ.ኤ.አ.) በ ሄግ፡ ኔዘርላንድስ ከተማ ውይይት አድርገው እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል:: ውይይቱ እንዲካሄድ የሆላንድ፡ የኖርዌይና የጀርመን መንግስታት በገንዘብ የረዱ መሆናቸውም ተገልጿል:: በውይይቱ ላይ ፕ/ር አኤፍሬም፡ ፓስተር ዳዓኤል እና አምባሳደር የተገኙ ሲሆን፡ ከ ኦነግ በኩል ደግሞ አቶ ለንጮ ለታ፡ አባ ቢያ አባ ጆቢር እና አቶ ዲማ ነጎ ተገግተው ከተወያዩ በሁዋላ ቀጣዩን ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ ማድረግ እንዳለባቸው ተስማምተው ተለያይተዋል::

ወያኔ ምርጫ 97ን በገሃድ ካጭበረበረ በሁዋላ በንጹሃን ዜጎች ላይ እራሱ የሚዘገንን ግፍ ፈጽሞ ሲያበቃ ወንጀሉን በቅንጅት መሪዎች፡ በነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞችና በሙያ ማህበራት መሪዎች ላይ ማመካኘቱ ለመላው አለም የአደባባይ ሚስጥር ነበር:: በተለይ ጉዳዩ እራሱ ባቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን በይፋ ሲጋለጥ ነበር ወያኔ ማጠፊያው ያጠረው::

በሃገር ውስጥ የነበረው ስር የሰደደ የኢኮኖሚ፡ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ መናጋት ያስከተለው አለመረጋጋት - በአንድ በኩል፡ ስርአቱ የውጭ እርዳታ ጥገኛም በመሆኑ የምእራባውያን ይደረግ የነበረው ግፊት - በሌላ በኩል፡ - ከዚያ ሁሉ በላይ ደግሞ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የመለስ ዜናዊን የጥገኛ ስርአት እረፍት እንደነሱት በኢህአዴግ ውስጥ ያሉትም ይመሰክራሉ::

በምርጫ 97 ሃገሪቱን እንዲመሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ስለመርጣቸው ብቻ በሃገር ክህደት ወንጀል ተከሰው ቃሊቲ ሲማቅቁ የነበሩ የህዝብ እንድራሴዎች ጋዜጠኞችና የሲቭክ ማህበር መሪዎችን ከነበሩበት የግፍ እስር ለማስፈታት ሚና ሲጫወቱ ከነበሩት ውስጥ የፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳቅ ስም በስፋት ይነሳል:: ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳቅ ታዋቂ ግለሰቦችን በማሰባሰብ፡ ከቤተ-መንግስት ቃሊቲ በመመላለስ በመጨረሻ እስረኞቹ እንዲፈቱ ጥረት አድርገዋል::

ፕሮፌሰር ኤፍሬም የሚመሩት የሽማግሌ ኮሚቴ ምንም እንኳን ጥረቱ ቢደነቅም በብዙዎች ሲተች ይሰማል:: ኮሚቴው ከሚደርስበት ትችት ዋናው፡ "ኮሚቴው አውቆትም ይሁን ሳያውቅ ይኢህአዴግን እድሜ ለማራዘም የተቋቋመ፡ የስራቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስብስብ ነው::" የሚለው ነው:: ይህንን ትችት የሚሰነዝሩት ሃይሎች እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ኮሚቴው የአቶ መለስ ስርአት ከፍተኛ ውጥረት ወስጥ በነበረበት ጊዜ ችግሮችን ለማብረድ ሲሯሯጥ መታየቱ ነው::

በዚያ ለአኢሃዴግ አስቸጋሪ በነበረበት ወቅት የቃሊቲ እስረኞች ፊርማቸውን እንዲያኖሩና ከእስር እንዲወጡ የሽማግሌው ኮሚቴ የገባቸው ቀል-ኪዳኖች (ቅድመ-ሁኔታዎች) ነበሩ:: ከነዚህም መካከል ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የፖለቲካ ውይይቱ እንደሚቀጥል ነበር:: ይህ አልሆነም::

እስረኞቹ ከቃሊቲ ከወጡ በሁዋላ የሽማግሌ ኮሚቴው በየመገናኛ ብዙሃኑ አቶ መለስን ከማመስገን ውጪ ችግሮቹ እንዲፈቱ ያደረጉት አንዳች ጥረት አልነበረም:: ይልቁንም የቅንጅት መሪዎችን በጋራ ሳይሆን በግል እየጠሩ የመከፋፈል ሚና ተጫውተዋል ተብሏል::

ኮሚቴው እውነተኛና ገለልተኛ ከሆነ ይህን ለምን እንዲሆን አላደረገም? ገዢው ፓርቲ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይሆን? ታዲያ ይህንኑ ለምን ለህዝብ ይፋ አያደርጉትም?

የቅንጅት ሰም "ከሜዳው ውጭ" በሆነበት በአሁኑ ወቅት የወያኔ አይን ያለው በኦነግ ላይ ይመስላል:: ኦነግንም "ከሜዳው ውጭ" ለማደረግ፣፣ የኦነግ አመራር ለሁለት በተከፈለበት ወቅት የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣውን መግላጭ ያስተውኋል::